በማግባት እና ርትዕን መሠረት በማድረግ ተገቢ ነው የሚለውን የጉዳት ካሣ ይወስንለት ብለን ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡

4. ተጠሪ ኃላፊነቱን ወስዶ ለ2ኛ አመልካች ሕክምና ተያያዥ ወጪ ይክፈል በሚል በከፍተኛው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ በበኩላችንም ተቀብለነዋል፡፡ አልተነካም፡፡
5. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የደረሰውን ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ



የሰበር መ/ቁ. 34906

ግንቦት 5 ቀን 2000 ዓ.ም

ዳኞች፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

መድኅን ኪሮስ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት ቤተልሄም ሲሣይ ቀረበች

**ተጠሪ፡-** ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቄ ቀረበች

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሐሰት ውንጀላዎችን የያዘ ደብዳቤ በመፃፉ ስሜ ጠፍቶአልና የሕሊና (የሞራል) ጉዳት ካሣ ይከፈለኝ በማለት ተጠሪ በመሠረተችው ክሥ መነሻነት የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ ክስ የመሠረተችው ታዬ ለማ በተባለ የድሬዳዋ ሪጂን ቴሌኮሙኒኬሽን ሥራ አስኪያጅ ላይ ሲሆን፣ ይህ ሰው ለክሱ በሰጠው መልስ ደብዳቤውን የፃፈው ከተጠሪ ጋር ባለው የግል ግንኙነት ሣይሆን፣ ከኮርፖሬሽኑ ሥራ ጋር በተያያዘ ጉዳይ መሆኑን በመግለጽ አመልካች በክርክሩ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባለት ጠይቋል፡፡ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ የሆነው በዚህ መሠረት ሲሆን አመልካች ለቀረበው ክስ የበኩሉን የመከላከያ ክርክር አቅርቧል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤት የሁሉንም ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኃላ፣ ተከሣሹን ከክሱ በማውጣት አመልካችን ኃላፊ አድርጎአል፡፡ በመቀጠልም አመልካች ብር 3000 ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔውን ያጸና ሲሆን የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ጥር 2 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪን በሚመለከት ለኮርፖሬሽኑ በአንድ የሥራ ኃላፊ በቀጥታ የተፃፈው ሪፖርት የስም ማጥፋት ነው በሚል አመልካች ካሣ እንዲከፍል መወሰኑ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለውን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ስሜን የሚያጠፋ ውንጀላ አለበት የምትለውን ደብዳቤ የፃፈው ሰው የሷ የበላይ ዐለቃ ወይም ኃላፊ ነው፡፡ ደብዳቤው የተፃፈው ደግሞ ለቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ዋና መሥሪያ ቤት ነው፡፡ እንግዲህ እዚህ ላይ የምናየው በቴሌኮሙኒከሽን ኮርፖሬሽን አደረጃጀት መሠረት የሪጂን ሥራ አሥኪያጅ በስሩ ሆና የምትሠራን ሠራተኛ (ተጠሪን) በሚመለከት የበላዩ ለሆነው ለዋናው መሥሪያ ቤት ደብዳቤ በቀጥታ መፃፉን ነው፡፡ አመልካች እና ደብዳቤውን የፃፈው ሰው በፍሬ ነገር ረገድ ያቀረቡት ክርክርም እንደተመለከትነው የበታች የሥራ ኃላፊ በሥሩ የሚያስተዳድራቸውን ሠራተኞች በሚመለከት ሪፖርት በዝርዝር በማቅረቡ የሠራተኞቹን ስም አጥፍቶአል ሊባል አይችልም የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ በደብዳቤዎቹ ላይ የሐሰት ውንጀላዎችን የሚያመለክቱ አገላለጾች አሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ የኔን ስም ለማጥፋት ተብሎ የገቡ ናቸው በማለት ተከራክራለች፡፡ የሥር ፍ/ቤቶችም ደብዳቤው የተጠሪን ስም የሚያጠፋ በእውነት ላይ ያልተመሠረተ አገላለጽን የያዘ ነው በማለት ነው አመልካች ካሣ እንዲከፍል የወሰኑት፡፡ ከላይ እንተደገለፀው ለደብዳቤው መፃፍ ዋና ምክንያት ሆኖ የሚታየው የሪጂኑ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ በሥራዋ የምታሣየውን ትክክል ያልሆነ ጠባይ እና ተገቢ አይደሉም የተባሉትን ድርጊቶችዋን በሚመለከት ለበላይ ኃላፊ ለማሣወቅ (ሪፖርት ለማድረግ) በመፈለጉ ነው፡፡ በእርግጥ በደብዳቤው ውስጥ ከተጠሪ



እይታ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የለውም ሊባል የሚችል አገላለጽ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ አይነቱ አፃፃፍ ተጠሪን ቅር የሚያሰኝ ቢሆን ደግሞ በዚያው በኮርፖሬሽኑ የበላይ ኃላፊዎች ታይቶ እልባት የሚሰጠው ነው የሚሆነው ፡፡ የሪጅኑ ሥራ አስኪያጅ ደብዳቤውን በቀጥታ የፃፈው ለበላይ መሥሪያ ቤት ኃላፊዎች እንጂ ከዚህ ውጪ ላሉት ማለትም ጉዳዩ ለማይመለከታቸው ወገኖች አይደለም፡፡ ይህ በራሱ የሚያሣየው ደግሞ የደብዳቤው ዓላማ ሪፖርት ከማቅረብ ውጪ መታየት የማይችል እንደሆነ ነው፡፡ በሪፖርቱ የተገለፀው ነገር እውነት ነው አይደለም የሚለው ደግሞ የሚወስነው ሪፖርቱ በቀረበለት የበላይ ኃላፊ ነው በመሆኑም በሥራ አስኪያጁ በተፃፈው ደብዳቤ ኃላፊነትን የሚያስከትል (የፍትሐብሔር) የስም ማጥፋት ድርጊት ተፈጽሞአል የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የሰጡት ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

<u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 8329 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 03295 ኅዳር 23 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348(1) መሠረት ተሸሯል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የሚከፍለው ካሣ የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ